# የአሜሪካ ፕሬዚደንትና ምክትል ፕሬዚደንት ምርጫ ሂደቶች በአሜሪካ

በአሜሪካ ሕግ ወይም ኮንስቲትዩቲሽን አንቀጽ 2 መሰረት ለአሜሪካ ፕሬዚደንትነት ወይም ምክትል ፕሬዚደንትነት እጩ ሆኖ ለመቅረብ፣ የአሜሪካ ዜጋ መሆን አለበት።ቢያንስ እድሜው 35 ዓመት የሆነውና በአሜሪካ ውስጥ 14 ዓመት ጨርሶ የኖረ አሜሪካዊው ሊሆን ይገባል። ሁለት ከሌሎቹ ጎልተው ሊጠቀሱ የሚገባቸው ተቅዋማት የፌደራል ኢሌክሽን ኮሚሽንና የፌደራል ኢሌክሽን ካምፔይን አክት የሚባሉት ናቸው።

ለአሜሪካ ፕሬዚደንትነት ወይም ምክትል ፕሬዚደንትነት ለመወዳደር የሚፈልግ የአሜሪካ ዜጋ በመጀመሪያ በፌደራል ኢሌክሽን ኮሚሽን መመዝገብ ገዴታው ነው። በሁለተኛ ደረጃ ለእጩው ራሱን ወይም ራሷን የምታስተዋውቅበት የገንዘብ እርዳታ የሚቀናጅበት የፌደራል ኢሌክሽን ካምፔይን አክት አማካይነት እንደሆነ ነው።

እጩዎች ከኮርፖሬትስ የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ እንዲቀርና እጩዎቹ ከኮርፖሬትስ ጥገኝነት ካልወጡ አብዛኛው የአሜሪካ ሕዝብ የሚጠቀምበት ፖለቲካ ምንግዜም ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችልና ለአንድ በመቶው ጥቂት ምርጦች የሚጠቅም ፖለቲካ ተግባራዊ እንደሚሆን የሚያምኑ ብዙ አሜሪካኖች እንዳሉ መግለጹ ተገቢ ነው።

አሁን ካሉት እጩዎች መሃከል ክሊንተን ዋናዋ የዋልስትሪት የገንዘብ እርዳታ ተቀባይ የሆነችና ስልጣን ላይ ብትወጣ የአንድ በመቶውን የጥቂቶቹን ምርጦች ፖለቲካ ተግባራዊ እንደምታደርግ ጸሃይ የሞቀው ሃቅ እንደሆነ ይታወቃል። የሪፓፐሊካንና የዴሞክራቲክ ፓርቲ እጩ ለመሆን የሪፓፐሊካን ፓርቲ የፕሬዚደንትነት እጩ ለመሆን የ 1191 ተወካዮችን ድምጽ ማግኘት ቅድመ ሁኔታ ነው።

በዴሞክራቲክ ፓርቲ ደግሞ የ 2118 ተወካዮችን ድምጽ ማግኘት ቅድመ ሁኔታ ነው። ኖሚኔቲንግ ፕሮሰስ ወይም የጥቆማ ሂደት ሁለት የጥቆማ ሂደቶች እንዳሉ ነው።እነርሱም አንደኛው ፕሬዚደንሺያል ፕራይመሪ ኢሌክሽንስና ካውኩሰስና ሁለተኛው ፕሬዚደንሺያል ኖሚኔቲንግ ኮንቬንሽንስ በአያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ የሚደርግ ጥቆማ ነው። ፕራይመሪ ኢሌክሽንስ የሚባለው በስቴትና ሎካል ገቨርንሜንትስ የሚካሄድ ነው። የካውካሰስ ጥቆማ የሚካሄደውና የሚዘጋጀው በፖለቲካ ፓርቲዎች ይሆናል። የተወስኑ ስቴቶች ፕራይመሪ ኢሌክሽንስ ሲያደርጉ፣ የተወሰኑት ደግሞ ካውካሰስ ኢሌክሽንስ ያደርጋሉ።

የተወሰኑት ደግሞ የሁለቱንም ድብልቅ ኢሌክሽንስ እንደሚያደርጉ ነው። ለምሳሌ Iowa state Caucus ሲጠቀም New Hampshire ደግሞ primary ን ይጠቀማል።ፕራይሜሪ ኢሌክሽንስና ካውካሰስ ኢሌክሽንስ ከፌደራል ምርጫው በፊት ከጀነዋሪ እስከ ጁን ባለው ግዜ ውስጥ በአጠቃላይ የሚካሄዱ ናቸው።ሁለቱም ፕራይሜሪስ ወይም ካውካሰስ ምርጫዎች ቀጥተኛ ያልሆኑ ምርጫዎች ናቸው።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ኖሚኔቲንግ ኮንቬንሽን ዋናዎቹ የአሜሪካን የፖለቲካ ፓርቲዎች ለፕሬዚደንትነት የሚቀርበውን እጩ በእያንዳንዳቸው ኖሚኔቲንግ ኮንቬንሽን ይመርጣሉ።ሁሉም ከፌደራል ምርጫው በፊት በበጋው ላይ ይከናወናል።በአያንዳንዱ ስቴት ባለው ሕግ መሰረትና በእያንዳንዱ ስቴት ባለው የፖለቲካ ፓርቲ ሕግ መሰረት፣ መራጮቹ መቼ እጩዎቹን እንደሚመርጡ በፕራይሜሪም ሆነ በካውካሰስ ምርጫ ተደንግጓል። እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ስንት ተወካዮች ለእያንዳንዱ ሲቴትና ቴሪቶሪ እንደሚሆን ይወስናል።

ለዚህም 1.እያንዳንዱ ስቴት የሰጠው ድምጽ ለዴሞክራትክ ፓርቲ ባለፉት ሶስት ምርጫዎችና 2.የኤሌክቶራል ቮትስ ቁጥር እያንዳንዱ ስቴት ያለው በማገናዘብ ይመድባሉ። ሪፓፐሊካንስ ፓርቲ በእያንዳንዱ ስቴት 10 ተወካዮች መድበዋል። በተጨማሪ በእያንዳንዱ ኮንግሬሽናል ዲስትሪክት 3 መድቧል። ልዩ ተወካዮች የተለየ ቅድመ ሁኔታ ያላቸው ስቴትና ቴሪቶሪስ አብረው የሚታዩበትም ሁኔታ ይኖራል። ስቴትና የአሜሪካ ቴሪቶሪ ተወካዮች ለሁለቱም ፓርቲዎች ኮንቬንሽንስ የተወሰኑ ተወካዮች በተጨማሪ ይመረጣሉ። ለሪፑፐሊካንስ ፓርቲ 3 ከፍተኛ የፓርቲው ባለስልጣናት ከእያንዳንዱ ስቴትና ቴሪቶሪ፣ ለዴሞክራትስ ሱፐር ዴሊጌትስ የፓርቲው ባለስልጣናትና የተመረጡ የመንግስት ባለስልጣናትን ይጨምራል።

እያንዳንዱ የፓርቲው ለፕሬዚደንትነት እጩ ሆነ የቀረበ ምክትል ፕሬዚደንት የሚሆነውን ይጠቁማል።አንድ እጩ የፓርቲውን ተወካዮች አብዛኛውን ድምጽ ማግኘት ካልቻለ፣ በ„ብሮከርድ ኮንቬንሽን“ እንደገና ምርጫው ይደገማል። ህዝባዊ ድምጽ ለመራጮች በምርጫው ቀን ኢሌክተርስ ለኢሌክቶራል ኮሌጅ ለመምረጥ የሚወሰነው በእያንዳንዱ ስቴት ሕግ መሰረት ነው። እያንዳንዱ ስቴት እስካሁን ኤሌክተርስን የሚመርጠው ሕዝቡ ነው። ሌላም አሰራር ይፈቀዳል።

ሁሉም ኤሌክተርስ በተመሳሳይ ቀን መሆን እንዳለበት የፌደራል ሕግ ደንግጓል።ይህም በኖቬምበር ወር ውስጥ ከመጀመሪያው ሰኞ ቀጥሎ ያለው ማክሰኞ እለት ይሆናል። ከኖቬምበር 2 በፊትና ከኖቬምበር 8 በኋላ ያለ ማክሰኞ መሆን የለበትም። ሕዝቡ የሚፈልገውን መራጭ መምረጥ ሕዝቡ የሚሰጠው ድምጽ ለፕሬዚደንትነት እጩ ለሆነው በቀጥታ ሳይሆን፣ ህዝቡ የሚሰጠው ድምጽ በቀጥታ ለኢሌክተርስ ወይም ለመራጮች ነው።ፕሬዚደንቱንና ምክትል ፕሬዚደንድቱን በቀጥታ የሚመርጡት ኢሌክተርስ ወይም መራጮች እንጂ ሕዝቡ አይደለም። ኤሌክቶራል ኮሌጅ በአንድ ስቴት አንድ እጩ አብዛኛውን ድምጽ ካገኘ፣ የተቃዋሚውንም ድምጽ አብሮ ይጠቀልላል።ለምሳሌ ዴሞክራት እጩ በዳላስ 60% የኢሌክተርስ ድምጽ ቢያገኝና ሪፑፐሊካንስ እጩ 40% ድምጽ ቢያገኝ፣ የዴሞክራቱ እጩ የዳላሱን 100% ይጠቀላላል ማለት ነው።

ኢሌክተርስ በየስቴቱ ሆነው የሚመረጡ ላሉት እጩ ድምጻቸውን ካልሰጡ በሕግ እንደሚቀጡ 24 ስቴትስ የየራሳቸውን ሕግ እንዳወጡ ነው። ሆኖም ግን በፌደራሉ ሕግ ኢሌክተርስ ለፈለጉት እጩ ድምጽ መስጠት እንድሚችሉ መብት ይሰጣቸዋል።የኤሌክተርስ ድምጽ ለፕሬዚደንቱና ምክትል ፕሬዚደንቱ በየስቴቱ ዋና ከተሞች በሁለተኛው ረቡዕ ዲሴምበር ወር ይሰጣል።በጀነዋሪ ጠቅላላ የኤሌክቶራል ኮሌጅ ድምጽ ቆጠራ በስኔቱ ምክትል ፕሬዚደንት ይከፈትና ተግባራዊ ይሆናል።

ከ 270 ድምጽ በታች እጩው ካገኘ፣ የድምጽ አሰጣጡ በሃውስ ኦፍ ሪፕሬዘንታቲቭስ ይካሄዳል።እያንዳንዱ ስቴት ለዚህ ምርጫ አንዳንድ ድምጽ ይኖረዋል።ምክትል ፕሬዚደንቱ በስኔቱ ይመረጣል፣ እያንዳንዱ የስኔት አባል አንድ ድምጽ ይኖረዋል።

ይህ ካልተሳካ ኮንግሬሱ ማን ፕሬዚደንት እንደሚሆን ይወስናል። የፓለቲካ ፓርቲ እጩ ምርጫ ከአጠቃላይ ምርጫ(ጄነራል ኢሌክሽን) ሂደት በፊት ዬትኛው እጩ የዬትኛው ፓለቲካ ፓርቲ እንደሚሆን ምርጫ በየፓርቲው ይካሄዳል።ይህም በየግዛቱ ደረጃ የተወከሉ ተወካዮች ለፕሬዚደንትነት እጩዎቹን ለፓርቲያቸው ይመርጣሉ።

የፓርቲዎች እጩዎች ምርጫ በየግዛታቸው የሚካሄድ ነው። ለዚህ እጩዎችን መራጮች ለመምረጥ ሁለት ዓይነት አሰራሮች አሉ።እነርሱም Caucuses ና primary ይባላሉ። Caucuses እጩዎችን ለመምረጥ የመጀመሪያው ነበር።በ 1900 ዎቹ primary አሰራር ከመጣ በኋላ ግን Caucuses ተፈላጊነቱ እየቀነሰ ሄዷል። Caucuses አሰራር ተግባራዊ በሚሆኑባቸው ግዛቶች አንድ ፓርቲ የሰብሰባውን ቀን፣ግዜና ቦታ መግለጽ አለበት።በአጠቃላይ ማንም መራጭ የሆነና በፓርቲው የመተዘገብ ማሳተፍ ይችላል። በ Caucuses አሰራር እጩዎች የግዛታቸውን ፍላጎቶች ወክለው እንዲቀርቡ የሚመረጡ ናቸው። ከውይይት በኋላ ተወካዮች ይመረጣሉ።

ፕራይሜሪና ካውከስ በ 20 ኛው መቶኛ ዓመት መጀመሪያ ላይ አንድ ለዜጎች ለፕሬዚደንትነት እጩዎችን በመምረጥ ደረጃ የተሻለ ስልጣን እንዲኖራቸው የሚያበረታታ እንቅስቃሴ ነበር። የ primary ምርጫ የተገኘው ከዚህ እንቅስቃሴ ነበር።በ primary ምርጫ የተመዘገቡ መራጮች እጩዎችን በምስጢር ይመርጣሉ።

ሁለት ዓይነት Primaries አሉ።ክፍትና የተዘጋ የሚባሉ ናቸው።open ና close primaries ማን ለመምረጥ መብት እንዳለው የሚወስንባቸው አሰራሮች ናቸው።በ closed primary መራጩ ለተመዘገበበት ፓርቲ መምረጥ የሚችልበት ነው። መራጩ እንደ ዴሞክራት ከተመዘገበ በዴሞክራቲክ prmary ብቻና የሪፑፐሊካኑም በሪፑፐሊካን primary ብቻ ይመርጣል። በ open primary መራጩ የዬትኛውም ፓርቲ አባል ቢሆንም የፈለገውን ፓርቲ እጩ መመረጥ ይችላል።መራጩ ከአንድ ግዜ በላይ መምረጥ ክልክል ነው።ሶስተኛው ዓይነት primary blanket primary የተመዘገበ መራጭ በሁሉም primaries መሳተፍ ይችላል።

የምርጫ ዝርዝር እጩዎቹን ወይም የተወካዮቹን ስም ዝርዝር አቀራረብ ላይ ልዩነት አለ።የፕሬዚደንታዊ ፕሬፈረንስ primary በቀጥታ አንዱን ለፕሬዚደንትነት ከቀረቡት መሃከል መራጩ የሚመርጥበት ነው።ሁለተኛው መራጩን የፓርቲ ተውካዮች ስም መሃከል አንዱን የሚመርጥበት ነው።በ caucus የተወካዮቹ የድጋፍ ድምጽ ለአንድ የፕሬዚደንትነት እጩ ወይም አለመምረጥ ነው።በአንዳንድ ግዛቶች caucus ና primary ን ይጠቀማሉ።

የዴሞክራቲክና የሪፖፐሊካን ፓርቲ ተወካዮች ምርጫ ፕሮፖርሽናል ዘዴ የሚባለውን አሰራር ዴሞክራቲክ ፓርቲ ይጠቀማል። ይህም ለምሳሌ አንድ ግዛት 10 ተወካዮችን 3 ለፕሬዚደንትነት እጩ ቢኖሩት፣ 60% ህዝብ እጩ X ን ቢደግፍ፣ እጩ Y ን 20% ቢደግፍና 20% ደግሞ Z ቢደግፍ፣ እጩ X 6 ድምጽ ይኖረዋል።እጩ Y ና እጩ Z ሁለት ሁለት ድምጽ ይኖራቸዋል።እያንዳንዱ ግዛት the winner-take-all method ወይም ፕሮፖርሽናል ሜተድ እንዲጠቀም የሚደነግግ ነው።

በዚህ አሰራር መሰረት ከፍተኛውን ድምጽ ያገኘው እጩ የግዛቱን ጠቅላላ ድምጽ ይኖረዋል።የ primary ምርጫ ከግዛት ወደ ግዛት በጣም ይለያያል። የመንግስት ጥገኝነት አንድ መንግስት የብዙሃኑ የአገሩ ህዝብ ጥገኛ ከሆነና ህዝቡ የሚፈልገውን ተግባራዊ እያደረገ ከሄደ፣ የብዙሃኑ ህዝብ ጥገኛ ነው ማለት ነው።ይህ ዓይነቱ መንግስት ህዝባዊና ዴሞክራሲያውም ነው።ምክንያቱም የአብዛኛውን ህዝብ ፍላጎት ተግባራዊ በማድረግ የሚንቀሳቀስ መንግስት ነው።አንድ መንግስት የጥቂቶችን ፍላጎቶች ተግባራዊ እያደረገ ከሄደ የአብዛኛውን ህዝብ ፍላጎት ሳይሆን የጥቂቶችን ፍላጎቶች የሚያረካ መንግስት ነው።

የዚህ ዓይነቱ መንግስት የጥቂቶች ሃብታሞች መንግስት ሲሆን፣ የጥቂቶች ጥገኛ የሆነ መንግስት ነው።ምሳሌ አሜሪካንን መጥቀስ ይቻላል። ግሎባላይዜሽን በግሎባላይዜሽኝ ስም የጥቂት ሃብታሞች ፍላጎቶች በዓለም ሕዝቦች ላይ በተለያዩ መንገዶች እየተጫኑ እንደሆነ እየታየ ነው። የሰራተኞችን ማህበራት በማፍረስ ሃይላቸውን በመበታታን ጥቂት ሃብታም ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደመወዝ የሰራተኞችን ጉልበት እየበዘበዙ የሚገኙበት ሂደት ላይ ነን።እነዚህ ጥቂት ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች የራሳቸው የሆኑ የነፍስ ገዳዮቹ ወታደሮች በወታደራዊ አገልግሎት ሰጪ ድርጅትነት ስም ሕጋዊ ኩባንያ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ፣ የአፍሪካንና እስያን የእርሻ መሬት በርካሽ ዋጋ የአካባቢ ነዋሪዎችን በግድ ካልሆነም በመግደል እያስለቀቁ እየገዙ ዓለምን ለመቆጣጠር ያላቸውን ህልም እውን እያደረጉ ነው።

በሶስተኛ ዓለም አገሮች ያሉ ወጣቶች የስራ እድላቸው በግሎባላይዜሽን ስም በአገራቸው መጥተው ስራቸውን የሚነጥቋቸውን ዓለም አቀፍ ኮርፖሬሽኖችን መቋቋም ስላልቻሉና ስራ የማግኘት እድል ስለሌላቸው አገራቸውን እየለቀቁ እየተሰደዱ ናቸው። የሰለላ ድርጅትና ሽብርተኝነት የስለላ ድርጅቶች ሽብሮችን መፍጠር ድብቅ ዓላማቸው ነው።ምክንያቱም ሽብር ከሌለ የእነርሱ መኖር አስፈላጊነቱ ይቀንሳል።ሲሆን ሲሆን ራሳቸው ወይም እነርሱ ለተለያዩ ሽብሮች የሚያዘጋጇቸው ግሩፖችን በመፍጠር፣ ሕዝብ ስጋት ውስጥ እንዲገባ በማድረግ፣ ሰላዮች፣ ፓሊሶችና ጦርነቶች እንዲጨምሩ የሚሆንበትን ሁኔታ ይፈጥራሉ።

የስለላ ድርጅቶች ለተለያዩ ዓላማዎች የሚያዘጋጇቸው ሃይሎች በተለያዩ የዓለም ክፍላት ይኖራሉ። ገንዘብ ማፍሰስ ብቻ ነው።ወንጀለኞች እንዲጠፉም ፍላጎታቸው ሊሆን አይችልም። የአሜሪካን ዴሞክራሲያዊ ትግል የአሜሪካን የዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ሲስተም ተበላሽቷል። ሲስተሙን ቀይሮ በአዲስ መልክ ህይወት እንዲኖረው ማድረግ የእያንዳንዱ ቅንና ዴሞክራት አሜሪካዊ ሃላፊነት ነው።ጥቂቶች በብዙሃኑ ሕዝብ ላይ የፈለጉትን የሚያደርጉበት ሁኔታ ላይ ናቸው።ሽብርን በማስፈራሪያነት እየተጠቀሙ ሕዝቡን ለጥቂቶች ዓላማ አመቺ ወደሆነው አቅጣጫ እያስቀየሩት ነው። እኔ እኔ የሚለውን የሰስታሞች አስተሳሰብ ከጭንቅላቱ አውጥቶ በመጣል 1% የሚገሙቱ የግፈኞችና ተንኮለኞች ሃብታም አሜሪካኖች ለማስቀየር ለትግሉ መዘጋጀት ብቻ ነው።

የአሜሪካ ፕሬዚደንትና ምክትል ፕሬዚደንት በህዝቡ በቀጥታ የሚመረጡ አይደለሙ።ህዝቡ አንድ „ዩ. ኤስ ኢሌክቶራል ኮሌጅ“ በመባል የሚታወቅ ተቅዋም አባል ሊሆኑ የሚገባቸውን የተወሰኑ ሰዎችን በአካባቢው ይመርጣል።እነዚህ የ„ዩ. ኤስ ኢሌክቶራል ኮሌጅ“ አባላት እንዲሆኑ የተመረጡት ሰዎች የአሜሪካን ፕሬዚደንትና ምክትል ፕሬዚደንት ለአራት ዓመት ይመርጣሉ።እነዚህ መራጮች በሁሉም የአሜሪካ ግዛቶች ውስጥ በየአካባቢው ህዝብ የሚመረጡ ናቸው።በየአካባቢው የመራጮች ቁጥር እንደ አካባቢው ግዛት ህዝብ ቁጥራቸው ይለያያል።

የ 538 መራጮች ምርጫ በአሜሪካ ሕግ መሰረት 538 መራጮች ከጠቅላላ የአሜሪካ ግዛቶች ይመረጣሉ።ከእያንዳንዱ የአሜሪካ ግዛት የሚመረጡት መራጮች ቁጥር ከ 3 እስከ 54 ይደርሳሉ።እነዚህ 538 መራጮች በቀጥታ በህዝብ የሚመረጡ ናቸው። ፕሬዚደንቱንና ምክትል ፕሬዚደንቱን የሚመርጡት እነዚህ በህዝብ በቀጥታ የተመረጡት 538 መራጮች ናቸው።መራጮቹ በየግዛታቸው በፖለቲካ ፓርቲዎችና ሌሎች ይጠቆማሉ።የአሜሪካ ሕዝብ በኖቬምበር ወር ውስጥ ከሰኞ ቀጥሎ በሚመጣ የመጀመሪያው ማክሰኞ ህዝቡ 538 መራጮችን በጠቅላላ አሜሪካ ይመርጣል። በህዝብ የተመረጡት መራጮች በየግዛታቸው በዲሴምብር ወር ውስጥ በሁለተኛው ረቡዕ በኋላ ባለው ማክሰኞ እለት ይሰበሰባሉ።

የመራጮቹ የምርጫ ውጤት ከኮንግሬስ ጋር በሚቀጥለው ዓመት ጀነዋሪ 6 ቀን በሚደረገው የጋራ ስብሰባ ይቆጠራሉ።ከ 538 ቱ መቀመጫ 270 መቀመጫዎችን ያገኘው አሸናፊ ነው።አብዛኛውን ድምጽ ያገኘ እጩ ምንም ከሌለ ፕሬዚደንቱ በተወካዮች ምክር ቤት ይመረጣል። የ 2016 ምርጫ አካሄድ ከኦገስት 2015 እስከ ማርች 2016 ድረስ የፕራይሜሪና ካውካሰስ ክርክሮች፣ ከፌብርዋሪ 1 አስከ ኦገስት 2016 ኖሚኔቲንግ ኮንቬንሽንስ ከሰፕቴምበር 2016 እስከ ኦክቶበር 2016 የፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ክርክሮች ኖቬምበር 8 ቀን 2016 የምርጫ ቀን ዲሴምበር 2016 ኢሌክተርስ ድምጻቸውን የሚሰጡበት ጀነዋሪ 2017 ኮንግሬስ የኢሌክተርስ ድምጽ የሚቆጥርበትና የሚያረጋግጥበት ነው።

ትንሳኤት በቃና

http://www.ethiopanorama.com